# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::" (ኢሳ 48 ÷ 17)
God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – hello@ethiogodslove.org

ሕዳር 1996 Nov. 2003 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል::" (ኢሳ 54÷13)
አዘጋጅ :- መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

# ሞግዚት (አሳዳጊ) mentor

"ሕፃኑ ሳሙኤል …በካሕኑ ዔሊ ሥር ሆኖ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበረ:: … ወጣቱ ሳሙኤልም እግዚአብሔርን እያገለገለ አደገ::" (1ኛ ሳሙኤል 2÷ 11 እና 21 አዲሱ ትርጉም)

"ወጣቱ ሳሙኤል በኤሊ የአመራር ሥልጣን ሥር ሆኖ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፤…" (1 ሳሙኤል 1÷1 አ ትርጉም)

"እግዚአብሔርም እንደገና ለሦስተኛ ጊዜ ሳሙኤልን ጠራው፤ሳሙኤልም ተነሥቶ ወደ ኤሊ በመሄድ እነሆ ስለ ጠራኸኝ መጥቼአለሁ አለው:: ከዚህም በኋላ ሳሙኤልን ይጠራ የነበረው እግዚአብሔር መሆኑን ዔሊ ተገነዘበ፤ ስለዚህም፡ ወደ መኝታህ ተመልሰህ ሂድ፤ እንደገናም የጠራህ እንደሆን ጌታ ሆይ! እነሆ እኔ አገልጋይህ እሰማለሁና ተናገር በለው፡- ሲል <u>ሳሙኤልን መከረው</u> …::" (1 ሳሙኤል 8-9)

"… በዕምነት ዕውነተኛ ልጄ ለሆነ ለጢሞቴዎስ፤… ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ÷ አስቀድሞ ስለ አንተ እንደ ተነገረው ትንቢት በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ ዘንድ ይህችን ትዕዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ፡…" (1 ጢሞቴዎስ 1÷ 2 እና 18)

በቀድሞ ዘመን ልዑላንና የመኳንንት ልጆች ለታላላቅ ኃላፊነታቸው የሚዘጋጁት በሞግዚት ርዳታ ነበር:: ዛሬም ቢሆን <u>ወጣትን ሰው ለሚጠብቀው ኃላፊነት÷የሚያስፈልገውን ትምሕርትና ሥልጠና አግኝቶ ማደጉን በማረጋገጥ የሚረዳ ሰው ሞግዚት ይባላል</u>:: አንዳንድ ጊዜ ሞግዚቶች ኰትኩተው ለሥልጣን ያበቁትን ሰው ሥልጣን ከያዘ በኋላም <u>አማካሪ</u> ሆነው ያገለግሉታል:: ሞግዚት ያልነውን (ሜንተር) የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል የእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት÷አስተዋይና የታቀመነ አማካሪ፡ ይለዋል::

በክርስትናችን ብዙ የማያስፈልጉ ችግሮች ውስጥ ሳያልፉ ለአገልግሎት የደረሱና በአገልግሎታቸውም የተሳካላቸው አገልጋዮች ታሪክ ቢመረመር÷ ዋናው ሚስጢራቸው ጥሩ መንፈሳዊ አባት (ሞግዚት) ስላላቸው ሆኖ እናገኛለን:: በመንፈሳዊ ሕይወት በሚታደግበት ወቅት÷የታመነ ወንድም÷ የተሰጠ መሪ÷ በፍቅር የሚያደፋፍርና የሚያጽናና ሰው ማግኘት እጅግ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: የሞግዚትን ጥቅም ብንረዳና ተግተን ብንፈልግ ማንኛችንም የዚህ መልካም ነገር ተጠቃሚዎች ልንሆን እንችላለን::

## የሞግዚት (mentor) ተጠቃሚ ለመሆን ራስን ለማዘጋጀት የሚረዱ ጥቂት ሐሳቦች እነሆ:-

★ሞግዚት የሚያስፈልግህ በተለይ በምን ላይ አተኩሮ ነው? ለአገልግሎትህ በሚያስፈልጉህ ነገሮች ከሚረዱህ ሰዎች ጋራ የሚያገናኝህ ሰው ነው? የሚያደፋፍርና የሚያበረታታ ሰው ነው? የሚያስተምርና የሚያስጠና ሰው ነው? የምታማክረውና የሚመራህ ሰው ነው? በመምራት አገልግሎት የተፈተነና ለመሪነት የሚያዘጋጅህ ሰው ነው?

★በሞግዚት የሚጠቀም ሰው ምን ምን ጠባዮች ሊኖሩት እንደሚገባው እወቅ፤ ለምሳሌ፡- የመማር ፍላጎትና ፈቃደኛነት ጨዋነት÷ ትጋት÷ ዕውነተኛነትና አለማስመሰል÷ ትሕትና÷ የሞግዚቱን ዕድሜ ልክ ተሞክሮና ብስለት ማክበር ናቸው:: እግዚአብሔር እነዚህን ባሕሪያት በአንተ ውስጥ እንዲያሳድግ ከአሁኑ ፀልይ::

★የራስህን መንፈሳዊ÷አዕምሮአዊና አካላዊ ሁኔታ በአግባቡ መርምረህ ተረዳ:: ጌታ ኢየሱስ ለአንተ ያለውን ያልተቆጠበ ፍቅር በማስተዋል÷ በሕይወትህ ለማደግ፡ የእርሱ ጸጋና እርሱን የሚወዱት ሰዎች ርዳታ እንደሚያስፈልግህ ተገንዘብ::

★ከባሕሪያትህ ሁሉ፡በተለይ የትኛውን ለማሳደግ እንደምትፈልግ ርግጠኛ ሁን:: እስከ ዛሬ ያለፍክባቸው ቀውጢዎች (crises) በባሕሪህ ላይ ያስከተሉትን ምልክቶች ወይም ተጽእኖ አስተውል:: የቀውጢዎቹም ጉዳት አሁንም ሳይፈወስ ካለ አስቀድመህ ለመፈወስ የሚረዳ ርምጃ መውሰድ ሊኖርብህ ይችላል:: በተጨማሪም፡- በአስተዳደግህ እግዚአብሔራዊ ባሕሪያትን ሳታይ አድገህ ከሆነ፡- ይህንን ጉድለት በማማከር (counceling) የሚያካክስልህ ሞግዚት ያስፈልግሃል::

★ከቤተሰብህ÷ ከጓደኞችህና ከሕብረሰብህ ጋር ያለህን ግንኙነት ጤናማነት አስተውል:: በማሕበራዊ አኗኗርህ እየተሻልህ እንድታድግ ሞግዚት እንዴት ሊረዳህ እንደሚችል አስብበት::

★ሞግዚትህ በዕድሜ ክልል ከአንተ የሚለይ ከሆነ÷ በአመለካከትም ከአንተ ሊለይ እንደሚችል አትዘንጋ:: ሞግዚት በመንፈሳዊ ብስለቱ የተሻለ መሆን አለበት እንጂ በዕድሜ ከአንተ የመብለጥ ግዴታ የለበትም:: በአመለካከቱም መሠረታዊ ባልሆኑ ነገሮች ላይ ከአንተ ሊለይ ይችላል:: ቢሆንም የሞግዚትን አስተሳሰብ ልብ አድርጎ ማስተዋልና መፈተን ጠቃሚ ነው::

★ሞግዚት እጅግ ተፈላጊ በሆኑት ነገሮች ጥራት ሊኖረው ይገባል:: ለምሳሌ፡- (ለጌታ ኢየሱስ ታማኝነቱ÷ርኅራኄውና የእግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰማ መሆኑ ወዘተ) በግልጽ ሊታወቅ ይገባል:: እንዲህ ያለ ተፈላጊ ሞግዚት ግን፡ ምናልባት አሁን በአካባቢህ ላይኖር ይችላል::ከዘመዶችህ ወይም አሁን ከምታውቃቸው ሰዎች አንዱ ላይሆንም ይችላል:: ይህንንም መረዳት የጌታን ምሪት እየለመኑ በትዕግሥት ለመጠባበቅ ይረዳል::

★ከሞግዚት ምን ውጤት እንደምትጠብቅ ወስን፤ ከዚያም፡ አጠባበቅህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መሆኑንና ስሜታዊ ብቻ አለመሆኑን ለይተህ ተረዳ:: ሞግዚቶችም ከአንተ የሚጠብቁት ነገር እንዳላቸው አትዘንጋ::

★በአካባቢህ ካሉትና ከምታገኛቸው ከሐከል የምታከብራቸውንና ሞግዚት ሊሆኑኝ ይችላሉ የምትላቸውን ሰዎች አስብ:: ለሞግዚትነት ከመጠየቅህም በፊት በፀሎት ጌታን ጠይቀው::እግዚአብሔር ከትክክለኛው ሞግዚትህ ጋር እንዲያገናኝህ ፀልይ:: የሚቀርቡህና የበሰሉ የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲጠቁሙህ መጠየቅም መልካም ነው::

★ሞግዚት ካገኘህ በኋላ አስቀድማችሁ ሁለታችሁ የምትስማሙበትን ቃል ኪዳን አድርጉ:: ከዚያም ኪዳናችሁ መጠበቁን የምትገመግሙበትን ቀጠሮ አድርጋችሁ በየጊዜው ወዳጅነታችሁ በደኅና መካሄዱን መመዘን ያስፈልጋችኋል::

★በዚህም ሁሉ፡- አንዱ የሌላኛውን ሚስጢርና ስሜት በጥንቃቄ ማክበርና መጠበቅ አለበት:: ዕውነትን መነጋገር÷ ፍቅርን መጠበቅና መከባበር መሠረታዊና ወሳኝ ናቸው::

(በሞግዚት ሥር ለማደግ መዘጋጀት ÷ ከተባለ መጽሐፍ ተወስዶ ከተዘጋጀ መልዕክት ተተረጎመ)

እንደ ልጁ ወይም እንደ ታናሽ ወንድሙ በፍቅር ኮትኩቶ የሚያሳድግህና ለእግዚአብሔር ክብር ፍሬአማነት የሚያደርስህ ሞግዚት ጌታ እግዚአብሔር ይስጥህ:: ለአንቺም::

የሚከተለውን ሥዕል በመመሪያው መሠረት ይመልከቱ:-(1ኛ) መካከል ላይ ያሉትን አራት ነጥቦች ለአርባ ደቂቃ ያክል አተኩረው ይመልከቱ፡ (2ኛ) ከዚያም በቅርብዎ ወዳለው ልስን ግድግዳ ይመልከቱ፤(3ኛ) ብሩህ ክበብ መታየት ይጀምራል:: (4) ዓይንዎን ጨፍነው ይግለጡና የሚታይዎትን ያስተውሉ:: (5) ማን ይታይዎታል? የሚታይዎትን ያውቁታል? ---------------------------------------------------



## መንግሥተ ሰማይ የማይገቡት እነ ማን ናቸው?

ዳግመኛ ያልተወለዱ፡-"ኢየሱስም መልሶ፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።" (የዮሐንስ ወንጌል 3፥3)

ከኢየሱስ ሌላ አዳኝ ያላቸው የሚመስላቸው፡- "በሩ እኔ ነኝ፡ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥..." (የዮሐንስ ወንጌል 10፥9)

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፡ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (የዮሐንስ ወንጌል 14፥6)

ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር "መዳን በሌላ በማንም የለም፡ እንድንበት ዘንድ የሚገባ ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።"
(የሐዋርያት ሥራ 4፥12)

በኢየሱስ ክርስቶስ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ያላመነ ግን ይፈረድበታል።" (የማርቆስ ወንጌል 16፥16)

በሥጋዊ ፍላጎት የሚመሩ፡- "የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው፡ እርሱም ዝሙት፥ርኩሰት፥ መዳራት፥ጣዖትን ማምለክ፥ምዋርት፥ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ቁጣ፥አድመኛነት፥መለያየት፥መናፍቅነት፥ምቀኝነት፥መግደል ስካር፥ዘፋኝነት፥ይህንም የሚመስል ነው።" (ወደ ገላትያ ሰዎች 5፥ 19 – 21)

## አማላጃችን ማን ነው?

"የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።"
(ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥34)

"እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፡ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፡ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን እንደ ሆነ ያውቃል፥እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳልና፡" (ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥ 26 – 27)

ጌታ ኢየሱስ "... ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከአመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፥ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ ፥ ስለ አመፀኞችም ማለደ።"
(ትንቢተ ኢሳይያስ 53፥12)

# የሕይወት ውኃ ወንዝ ወይስ ኩሬ

ባለቁ ቁጥር እንደገና እየተሞሉ የሚሠሩ ባትሪዎችን የማያውቅ ሰው ብዙ አይመስለንም። እነዚህ (ሪቻርጀብል) ወይም መላልሰው የሚሞሉ በመባል የሚታወቁት ባትሪዎች፡- እንደሚፈለግባቸው ሊሠሩ የሚችሉት፡ በየጊዜው ኃይላቸው እስኪሟጠጥ ድረስ ከተሠራባቸው በኋላ፥እንደገና ከተሞሉ ነው። የባትሪው ጠቃሚነትና ዕድሜ የሚረዝመው ኃይሉ እስኪሟጠጥ በመሥራቱና መልሶ በመሞላቱ ነው ነገር ግን ባትሪውን በኮሬንቲ ሙልት አድርጎ፥ ያለ ሥራ ማስቀመጥ ለወደፊት ከጥቅም ውጭ የሚያደርገው ዓይነተኛ ስሕተት ነው።

ብዙ ክርስቲያኖች ተሞልቶ ተሞልቶ በመደርደሪያ ላይ እንደተጎለተ ባትሪ ናቸው።በየዕሑዱ ቤተ ክርስቲያን በመገኘት በቃሉና በመንፈሱ ይሞላሉ። ቢያንስ በሳምንት አንዴ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቦታ በመገኘት፥መንፈሳዊ ሙዚቃዎችን በማዳመጥና መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ፡- በእግዚአብሔር ኃይል ይሞላሉ። ነገር ግን የሞላው ባትሪአቸው በሥራ (አገልግሎት) ላይ ባለመዋሉ ምክንያት ኃይሉ አይጎድልም። የኃይል ኩሬ እንደ መሆን ማለት ነው። የተሞላ ነገር የሚጎድልበት መንገድ ካልተገኘ በቀር እንደገና በአዲስ ኃይል ሊሞላ እንዴት ይችላል? ፈጽሞ አይችልም። ለዚህ ነው ጌታ በዮሐንስ ወንጌል 7፥38 "በእኔ የሚያምን፥መጽሐፍ እንዳለ፥የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል፡"ያለው። እንግዲህ የወንዝና የኩሬ ልዩነት ይታያችሁ። አንዱ በሞላ መጠን አልፎ የሚፈስስ ሲሆን፥ ሌላኛው ደግሞ ሞልቶ የሚቀመጥ ነው። በጤናማነትም የሚፈስሰው (የወንዝ ውኃ) ሞልቶ ከሚቀመጠው የኩሬ ወኃ ይበልጥ ጤናማ ነው።

የአገልጋይነት ልብ ሊኖረን ይገባል። የተሞላነውን የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ቅዱስ፡- ባለመታከት ወደ ሌሎች ሰዎች ማፍሰስ አለብን። ይህም ማለት ለራሳችን የግል ጊዜና ዕረፍት አያስፈልገንም ማለት አይደለም። ጌታ ኢየሱስም በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት አልፎ አልፎ ከድካሙ ለማረፍና ለመጸለይ ለብቻው የሆነበት ጊዜ ነበረ።እንደ ዕውነቱ ከሆነ፡- አካላዊ ዕረፍትና የመንፈሳዊ ተሐድሶ አስፈላጊነት ልክ እንደ ባትሪው፡ በጎደለ መጠን ተመልሶ መሞላት አስፈላጊ ነው። ሥራ የፈታ ባትሪ ያለ ቀኑ ሻግቶ እንደሚበላሽ ሁሉ፥ ከተሠራበት በኋላ ተመልሶ የማይሞላውም ባትሪ ለማንም ሊጠቅም አይችልም፡

ጌታችን ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣበትን ምክንያት ሲያስረዳ፡-"... የሰው ልጅ ሊያገለግል፡ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።"ብሎአል። በምድራዊ አገልግሎቱም ጌታ ሆኖ እያለ፥የተከታዮቹን እግር እንኳ እስከ ማጠብ ድረስ ወርዶ ራስን በአገልግሎት ማዋረድን አስተምሯል። ደግሞም እናንተም እንዲሁ አድርጉ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶአል። ይህንንም ትምሕርት የሚለማመዱ የእግዚአብሔር ቤት አገልጋዮች በአጸፋው ሳይገለገሉና ሳይካሱ አይቀሩም።

ሌሎችን የማገልገል ትጋት ስናሳይ ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ። አንደኛ ትኩረታችን ይለወጣል። ተፈጥሮአዊ ባሕሪያችን ራስ ወዳድነት ስለ ሆነ፥ ሌሎችን ለማገልገል ስንወስን ትኩረታችን መለወጡ የማይቀር ነው። ይህን ሳናደርግ ቀርተን በተፈጥሮ ባሕሪያችን መሠረት በራሳችን ጥቅምና ምቾት ብቻ ላይ ብናተኩር ግን መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ጌታ ክርስቶስን ለዓለም እንዳይገልጽ ዕድል እንነፍገዋለን።

የጌታ ኢየሱስን ወደ ዓለም አመጣጥ እስቲ እንመልከት። በፊልጵስዩስ ምዕራፍ ሁለት እንደምናነበው፥ ጌታ በራሱ ፈቃድ ፥ ክብሩን ትቶ መጥቶ ፥ ራሱን አዋርዶ የታዘዘ መሆኑን እናያለን። "... እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ፡" ተብሎ የተጻፈውም በዚህው ምዕራፍ በቁጥር 4 ነው። አያችሁ? ጌታችን ከሰማይ ወደ ምድር መምጣቱ፥ክብሩንና ምቾቱን ትቶ ነው። ትኩረቱን ከራሱ ላይ ወደ ሰው ልጆች፡- እንዲሁም ከሰማይ ወደ ምድር ማዞሩ ነው። በፊልጵስዩስ 2፥5 ደግሞ "በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።"በማለት በአገልጋይነት የጌታን ፈለግ እንድንከተል ያስተምረናል።

ሁለተኛው፡- ትኩረታችንን ስንለውጥ ራሳችን እንለወጣለን።እግዚአበሔርንና ሕዝቡን ለማገልገል አስፈላጊ የሆኑት፡- እንደ ጸጋ፥ የመንፈስ ተሐድሶ፥ቅባትና ራዕይ ያሉት ነገሮች ለአገልግሎት ራሳችንን ስናቀርብ ስለሚሰጡን ራሳችን እንለወጣለን። አገልጋይነት የአገልጋዩን ማንነት ለመልካም ይለውጣል።ያበጃል፡

"ጌታውም መልካም ነው! አንተ ታማኝና ደግ አገልጋይ፥ በጥቂት ነገር ታማኝ ሆነህ ስለተገኘህ በብዙ ነገር ላይ እሾመሃለሁ፥ና፡- የጌታህን ደስታ ለመካፈል ግባ ! አለው"
(የማቴዎስ ወንጌል 25፥23 አዲሱ ትርጉም)

"ጌታው ከሄደበት ሲመለስ ልክ እንደ ታዘዘው ሲፈጽም የሚያገኘው አገልጋይ እንዴት የተመሰገነ ነው! በእውነት እላችኋለሁ፥ ጌታው ያን አገልጋይ የንብረቱ ሁሉ ኃላፊ አድርጎ ይሾመዋል።"
(የሉቃስ ወንጌል አዲሱ ትርጉም 12፥ 43 – 44)

(ዴቭድ ጀረማያ ሌሎችን ማገልገል በሚል ከጻፈው ተወስዶ የተዘጋጀ)

## ምሥጋና

እሕታችን ወይዘሮ መነን ተሰማ ከኦቨርላንድ ፓርክ፡ ካንሳስ፡- ስላደረጉልን የገንዘብ ድጋፍ በጣም እናመሰግናለን። ጌታ አብዝቶ ይባርክዎት።

www.ethiogodslove.org
ስለ ዌብ ገጻችን አስተያየት አለዎት? የገጹ ግንባታ እየተጠናቀቀ ስለ ሆነ፥ አስተያየታችሁንና ምክራችሁን ለግሱን። ጌታ ይባርካችሁ።

## እስፖንሰር

አገልግሎታችን ጠቃሚ ነው? ከሆነ በየትኛውም ሐገር የሚኖር ዘመድ፥ ወዳጅ ወይም ጓደኞች ካለዎት፥ አድራሻቸውን ይላኩልን። ከቻሉም የፖስታውን ዋጋ ጨምረው ይላኩልንና በየወሩ በቋሚነት እንልክላቸዋለን።

በአሁኑ ወቅት ደብዳቤአችን በሰሜን አሜሪካ በሰፊው፥በአውሮፓ፥በአውስትረሊያ፥ በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ በመጠኑ ይሰራጫል። ዓለም አቀፍ የፖስታ ዋጋ፡- በዓመት $9.60 USD ነው። ለሁለት ደብዳቤ $19.20 ብቻ መሆኑ ነው።ይህም ለሃምሣ ሰው እንደ ሃምሣ ሎሚ ይሆናል ማለት ነው። ኢየሱስ ጌታ ነው። ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (የዮሐንስ ወንጌል 3 ፥ 23)